# የባሕል ደግና መጥፎ...

በግልጽ እንነጋገር ከተባለ፣ ማንም ኢትዮጵያዊ በሃገሩና በባሕሉ ሲኮራና ሲመካ እንጂ ሲያፍርበት አይሰማም። ይህም በመሰረቱ ደግ ቢሆንም እንኳን፣ ጉዳዩን እስኪ በግልጽ እንመልከተው። ባሕላችንን ሁሉ በጭፍን ግሩም ነው እያልን ከማድነቅና በኩራት ከመንቀባረር ይልቅስ፣ እያንዳንዱን ሆን ብለን በጥሞና ብንመለከትና ብናጠናው መልካሙንና ደግ ያልሆነውን ለማወቅ፣ አበጥረንም ለመለየት እንችላለን።

መልካሙንና መጥፎውን ለይተን ካወቅን የሚጠቅመውን አጥብቀን ይዘን እንድንኮራበት፣ የማይጠቅመውንም ለማስወግድ እንችል ይሆናል። ይህ መድረክ ለሌሎች ጸሓፊዎችም፣ ኢትዮጵያውን ቢሆኑም ባይሆኑም እንዲሳተፉና ያዩትን፣ የሰሙትን፣ የደረሰባቸውንም እንዲጽፉና እንዲተቹም እጋብዛለሁ። መደማመጥና መተራረም ብዙ መልካም ፍሬ ሲኖረው፣ መጥፎ ባሕልን አምቆና ደብቆ መያዝ ግን ጉዳት እንጂ ጥቅም የለውም።

ከተለያዩ ሰዎች አስተያየትና አመለካከት ብዙ ቁም-ነገር ስለሚገኝ፣ ሁላችንም የባሕላችን ጉድለቶችን አንድ በአንድ እንስተን እንድንነጋገርባቸውና እንድንተችባቸው፣ መልካም የሆኑትን በምን መንገድ እንደምናጐለብታቸው፣ መልካም ያልሆኑትን ደግሞ እንዴት እንደምናስወግዳቸው ከልብ “ኑ! እንነጋገር” እያልኩ እጋብዛለሁ።

1) ሰለ ይሉኝታ - ሰው ይሉኝታ ከሌለው ከከብት በምንም አይሻልም ለማለት ይቻላል። ስለዚህ ማንም ሰው ይሉኝታ እንዲኖረው ተገቢ ነው። ይሉኝታ ግን ከመጠን አልፎ ሲበዛ፣ ሰው በልቡ የሚያምነውን ጥልቅ ነገር ደብቆ ይዞ፣ በይሉኝታ ገመድ ታስሮ የሚያምንበትን ሳይገልጽ፣ ባመነበትም ሳይጸና ከቀረ ምን ዋጋ አለው? እንግዲያውስ ይሉኝታም መጠን እንዲኖረው ይገባል። ካልሆነ፣ ሰው ምን ይለኛል እያሉ ከንቱ ጦም ማደር፣ ወይም ቆሞ መቅረት ነው ትርፉ። ይህም ጉዳት እንጂ ጥቅም የለውም።

ይሉኝታ ሰንሰለት አይቆራኝብን
ወደኋላ ቀርተን ቀኑ እንዳይመሽብን...

2) ቀጠሮ ስለ ማክበር - በብዙ የሰርግ ጥሪ ወረቀቶች “ከምሽቱ 8 ሰዓት ለእራት እንዲገኙልን...” የሚሉ ግብዣዎች አሉ። ይባስ ብሎም፤ “Please be on time.“ “በጊዜ እንዲገኙልን አደራ!” የሚል ማሳሰብያ ጭምር ያዘለ ነው። ይሁንና በተባለው ሰዓት በቦታው ቢሄዱ ጭር ያለ ቦታ ነው። ሰርገኞቹ ሙሽሮቹን አጅበው ከምሽቱ 11 ሰዓት ላይ “ጉሮ ወሸባዬ” እያሉ ወደ ዳስ ሲገቡ፣ እራት የሚቀርበው ወደ እኩለ ሌሊት ገደማ ነው። ይህም ሁኔታ በአሜሪካ ተደጋግሞ ይታያል። ቀጠሮ አክባሪነት በሃገራችን አጥብቆ እየተለመደ በመጣበት ዘመን፣ አሜሪካ ያለነው፣ ምሁራን ነን ባዮች፣ ምነው ቀጠሮ ማክበር ያቅተናል? መልሱ አጉል ልማድ... ነዋ!

ይህ ሁኔታ ሊለወጥ ይገባዋል። እራት እኩለ ሌሊት የሚቀርብ ከሆነ የጥሪውም ወረቀት ለእኩለ ሌሊት ተብሎ ይታረም። ካልሆነ ግን እራት ብሉ ተብሎ ጥሪ በተላከበት ሰዓት እራቱንም በወቅቱ ማቅረብ ይገባል። “ለ 8 ሰዓት እራት ድረሱ፣ አደራ” ብለው ሲያበቁ፣ እስከ እኩለ ሌሊት ሰውን አጉል ማስጠበቅና በረሃብ አለንጋ መግረፍ ተገቢ ነው ወይ?

በፊደላት ጥፊት እቴ ተጠንቀቂ
ቀ-ንን አጠር አርገሽ፣ ና-ንም እንድታውቂ…

እንግዲያውስ ለዛሬው እዚሁ ላቁም። ሌሎች አንባቢዎች የሚሉትንና የሚጽፉትን ለመስማት እጠባበቃለሁ። መታረም ስላለባቸው ብቻ ሳይሆን መልካም ስለሆኑት ልማዶችም አሞጋግሶ መጻፉ ተገቢ ነው።

ገ/ኢ. ጕርፉ።